# ኪ ዳ ና ች ን

# KIDANACH'N


**ልዩ ዕትም      መስከረም ፩ ቀን፥ ፳፻፲፩ (፯ሺ፲፩) ዓመተ ምሕረት**

**Special Edition**   **Meskerem 1, 2011 A.D (September 11, 2018)**


**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥**
**ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና**
**የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ልጆች የኾነውንም ኹሉ፡ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡**
**በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም።**

**Published by "Ethiopia: The Kingdom of God"**
**to reveal the Divine Truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God**
**and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;**
**and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.**

# የ፯ሺ፲፩ (፳፻፲፩) ዓመተ ምሕረት፡ ቀን መቍጠሪያ

## 2011 (2018-2019 Gregorian) Calendar


**አዘጋጅ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ።**



ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ-ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

**The Triumphant Lion of the Tribe of Judah**
**God The Son Jesus Christ**
**Eternal Priest in the Order of Melke-Zedeq the Ethiopian**
**King of Zion and King of Kings of Ethiopia**

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

**Ethiopia Reachs out Her Hands to God**
**Goddess The Mother Virgin Mary**
**Mother of Our Messiah and Our Holy Mother**
**Queen of Sovereigns of Zion and Ethiopia**

# <u>ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት</u>

# ልዑል እግዚአብሔር፡

## ከዘመነ ማርቆስ፡ ወደዘመነ ሉቃስ አሸጋግሮ፡
## የኢትዮጵያን የነጻነት ህልውና በዓላችንን፡ ፯ሺ፭፻፲፩ኛ ዓመት፥

እና

## የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፡ ፪ሺ፳፯ኛ ዓመት፥
## የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ፪ሺ፲፩ኛ ዓመት፡
## የትስብእት ልደታት በዓሎቻችንን፡ ለማክበር ለበቃንበት፡
## ለዲሱ፡ የ፪ሺ፲፩ (፳፻፲፩) ዓመተ ምሕረት፡
## እንኳን አደረሰን!

\+ \+ \+

## ስለቀን መቁጠሪያው መግለጫ።

፩ኛ፡- ይህ የቀን መቍጠሪያ የተዘጋጀው፡ "**ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!**" በሚለው፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም፣ ፳፻፱ ዓ.ም. እና ፳፻፲ ዓ. ም. በታተመው መጽሓፍ ውስጥ የተገለጹትንና አግባብነት ያላቸውን ሓተታዎች መሠረት በማድረግ ነው።

፪ኛ፡- "**በዘንዜከር**" በተባለው፡ የየዕለቱ የጸሎት መግቢያ፡ ለመዓልቱና ለሌሊቱ ቅመራ፡ መነሻ ኾኖ፡ ከሌሎቹ ቍጥሮች ጋር የሚደመረው **የ፳፻፲፩ቱ (የዕሥራ ምእት ዐሥርቱ ወአሓዱ) [የ፪ሺ፲፩ኛው] ዓመተ ምሕረት፡ ዓበቅቴው፡ ፳፭ [ኻያ-አምስት]፥ መጥቅዑ፡ ፭ [ አምስት]** ኾኗል።

፫ኛ፡- በቀን መቍጠሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ፡ በስም ብቻ የተጠቀሱት፡ ቅዱሳንና ቅዱሳት ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፡ ሌላ መግለጫ ካልተሰጠ በቀር፡ **ዕረፍታቸውን፥ የአኀዞቹ** [የቍጥሮቹ] የተለያዩ ቀለማት ደግሞ፡ ከዚህ የሚከተሉትን አብነቶች ያመለክታሉ፡-

ሀ. ቀዩ፡ **ዕለተ-ሰንበትን** *["ቅዳሜ" ስትባል የኖረችውን]፣* **ዕለተ-ሰንበት ዝልፍትን** [በ"እሑድ" የቀጠለችውን "ዘላለማዊቷን ሰንበት" (ዝልፍት)]፥ ዓበይት በዓላትንና ተከታታዮቹን የፍስክ ዕለታትና ሳምንታት፣

በ. አረንጓዴው፡ ንኡሳን በዓላትን፣

ገ. ሰማያዊው፡ የአጽዋማት ቀኖችንና ሳምንቶችን የሚያሳዩ ናቸው።

፬ኛ፡- **መስከረም ፩ ቀን፡-**

❖ምናልባት፡ በእየራሳችን ድክመትና ስሕተት፥ ጉድለትና ጥፋት፡ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊም ኹለንተናችንን፡ ያሳደፍንበትና ያበላሸንበት፥ ያሰነካከልንበትና ያስረጀንበት፡ አካላዊና ባሕርያዊ የኾነ፡ የአምልኮ ምንዝርና ግብር ቢኖር፡ ያን ኹሉ፡ የርኵሰትና የልክስክስነት ግብስብስና ዝባዝንኬ፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ፈጽመን፡ ከሰውነታችን በማስወገድ፡ ወዲያ አውጥተንና አሽቀንጥረን ጥለን፣ ኹለንተናችንን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች አንጽተን ያደስንባት፣

❖ከዚህም ጋር፡ ቅዱስ ቁርባናችን በኾነው፡ በሥጋ ወደሙ፡ ኹለንተናችንን ቀድሰን፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን፥ መንፈሳችንንም፡ ለእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም እና ለልጇ ለወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የልደታት በዓላችን ክብር ያበቃንባት፣

❖ሰላማችንን ያስገኘልን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ድኅነትን [መዳንን] ካስገኘችልን፡ ከእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ በቅዱሱ ኪዳን የተጐናጸፍነውንና የተቀዳጀነውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል፡ እንደዓዲስ ተሿሚና ተሸላሚ ባለድል የተቀበልንባት፣

❖ከአሮጌው፡ ወደዓዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ትንሿን ትርፍ የጳጉሜን ወር፡ በንስሓ፥ በጋድ ጾምነትና ንኡስ ሱባዔነት፡ የምስጋና ጾምና ጸሎት አድርገን ያሳለፍንላት መኾኗ ሊዘከር [ሊታሰብ] ይገባል።

፭ኛ፡- በቀን መቍጠሪያው፡ እያንዳንዱ ሠንጠረዥ ግርጌ፡ ለየወሩ የተመደቡ ምንባቦች ተሰናድተዋል። እነዚህ ምንባቦች የተዘጋጁት፡ በሳምንቱ የሥራ ቀኖች፡ በየዕለቱ፡ ለጧትና ለማታ፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ምዕራፎችን፥ እንዲሁም፡ በየሰንበታቱ፥ በሌሎቹም፡ የበዓላትና የዕረፍት ጊዜያት፡ በተቻለ መጠን፡ ምዕራፎቹን ጨማምሮ በማንበብ፡ ከቃለ-እግዚአብሔር ዝክረ-ነገር ላለመራቅ እንደሚቻል በመገመት ነው። መዝሙረ ዳዊት፡ በየቀኑ፡ በጸሎት መልክ ስለሚደገም፡ በምንባቡ ውስጥ አልታከለም፤ አልተካተተም።

፫ኛ፡- ጾሙና ጸሎቱ፥ የሱባዔው ጭምር፥ ምንባቡም፡ በግል፥ በቤተሰብ፥ ወይም፡ በኅብረት በመሰባሰብ ሊካኼድ ይቻላል።

፲ኛ፡- ይህን የቀን መቍጠሪያ፣ እንዲሁም፡ "**አዳምና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!**" በሚል፡ ዓቢይ ርእስ ሥር፡ "**አንደኛ መጽሓፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በጦብያ ፍለጋ!**"፥"**ኹለተኛ መጽሓፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በእውነት ፍለጋ!**" እና "**ሦስተኛ መጽሓፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በእውቀት ፍለጋ!**" በተጨማሪም፡ በኢትዮጵያኛ እና በእንግሊዝኛ የተዘጋጁ፡ «**የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ትምህርት፡ ለኢትዮጵያ ሕፃናት፤ "አንደኛ እና ኹለተኛ መጻሕፍት"**» የሚል ኣርእስት ያላቸውን ዕትሞች እና እየታተሙ ያሉትን፥ ደግሞም፡ "**ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ፤ ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት።**" ከእነዚህ በቀር፡ "**ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት**" በሚል አጠቃላይ ኣርእስት ሥር፡ "**ኣንደኛ መጽሓፍ**"፥ "**ኹለተኛ መጽሓፍ**" እና "**ሦስተኛ መጽሓፍ**" ተብለው፡ በተከታታይ የወጡትን፥ እንዲሁም፡ ቀደም ብለው፡ "**ምናሴ፡ የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!**"፥ "**ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!**"፥ "**ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!**" እና **Ethiopia: The Classic Case** በሚሉ ኣርእስት፣ እነዚህ ኹሉ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፥ ኣንዳንዶቹም፡ ለኹለተኛና ሦስተኛ ጊዜያት ታትመው የወጡትንና እየተሠራጩ ያሉትን፥ ሌሎችንም፡ ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን ዕትሞችና መጻሕፍት ለማግኘት፡ የጎዋ ሰሌዳችንን መጎብኘት፥ እንዲሁም፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ ባሳታሚው ኣድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።


**ወኪል አከፋፋይ፡- ዋሽራ መጻሕፍት ቤት። ስልክ ቁጥር፡-**

*0፱፻፲፩-፷፫ ፶፪ ፳፭* (0911-63 52 25) **እና** *0፱፻፲-፺፪ ፵፱ ፸፩* (0910-92 49 71)።

**አሳታሚ እና አከፋፋይ**

Publisher & Distributor

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።**

**Ethiopia: The Kingdom of God.**

*መልእክት ሣጥን ቍጥር፡ ፰፻፲፪።* P. O. Box 812.

**ስልክ ቍጥር፡-** *0፲፩-፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና 0፲፩-፰-፵-0፰-፴፬፤*

Tel.:- (011-4-16-18-85 & 011-8-40-08-34)፤

**የኪስ ስልክ ቍጥር፡-** *0፱፻፵፬-፩0 ፳፫ ፷፰ እና 0፱፻፲፩-፷፰ ፵፬ ፶፪፤ እና 0፱፻፲፩-፷፩ ፲፭ ፹፫ እና 0፱፻፳-፹፬ ፹፰ ፲፯ እና 0፱፻፳፱-፲፯ ፵፬ ፶፭*

Cellphone:- (0944-10 23 68 & 0911 68 44 52 & 0911 61 15 83 & 0920 84 88 17 & 0929 17 44 55)

**አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።** Addis Abeba, ETHIOPIA

*ወይም* or

**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**

**Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971**

Cellphone: 310-948-1024, 202-262-0230 & 202-262- 0713

Email: info@ethkogserv.org Web Site: www.ethiopiathekingdomofgod.org

Facebook: ethiopiathekingdomofgod


\+ + +

## ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ መስከረም ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of Meskerem (Sept.-Oct., 2018). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበተ ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- *ከቅዱሱ ኪዳን፡ ለሰውዘር፡የመጨረሻ፡ የማንቂያ እና የማስጠንቀቂያ ደወል፡ በኒው-ዮርኩ የ፲፱፻፺፩ዓ.ም. የቃጠሎ ግድያና ዕልቂት የተሰማባት፡ መስከረም ፩። (9/11) | | ፩ 11*<br>የድንግል ማርያም እና የኢየሱስ መሲሕ ልደታት።<br>የኢትዮጵያ ነጻነት። ኪዳነ ኣዳም ወሔዋን።<br>ቅዱስ ራጉኤል ሊቀ መላእክት።<br>ቅዱስ ዮሓንስ መጥምቅ።<br>በርተሎሜዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ። | ፪ 12<br>ዮሓንስ መጥምቅ | ፫ 13<br>ገዳማዊ አንበስ ኢትዮጵያዊ | ፬ 14 | ፭ 15<br>ሄሮድስ የፈጃቸው ሕፃናት። የአሕመድ ግራኝን ወረራ፡ በሃይማኖት ጽናት ተቋቁሞ የተጋደለ፡ አጼ ንብለ-ድንግል |
| ፮ 16<br>ኢሳይያስ ነቢይ | ፯ 17<br>ኢትዮጵያዊቷ ኤልሣቤጥ፡የመጥ ምቁ ዮሓንስ እናት። መናኔ-መንግሥት፡ኣጼ ተክለ-ሃይማኖት | ፰ 8<br>ግዝረተ-ኢየሱስ | ፱ 19 | ፲ 20<br>አጼ መስቀል።<br>ግማደ-መስቀሉ፡ በ፲፩ኛው ፻ዓመት በ፩ኛ አጼ ዳዊት፡ ወደኢትዮጵያ ስለገባ፡ "አጼ መስቀል" ተባለ። | ፲፩ 21<br>አጼ በካፋ፡ ስመ-ጥሩው ምሁር መሪ | ፲፪ 22<br>ስለንስጥሮስ ኑፋቄ፡ የ፪፻ ሊቃውንት ጉባኤ፡ በኤፌሶን |
| ፲፫ 23 | ፲፬ 24 | ፲፭ 25 | ፲፮ 26<br>ኪዳነ-ኖኅ። ደመራ።(ለመስቀል በዓል ዋዜማ፡ ለችቦ እሳት የዛፍ ኣጣኖችን መደማመር) | ፲፯ 27<br>መስቀል።<br>ኢየሱስ መሲሕ የተሠዋበት እውነተኛው መስቀል ተገኘ። | ፲፰ 28<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ኤዎስጣቴዎስ ስለቅዳሜ ሰንበትነት ተከራክሮ ረታ። | ፲፱ 29 |
| ፳ 30<br>የኢትዮጵያ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስክር የኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ (የአኵስም ንቡረ-እድ) ዕረፍት። | ፳፩ 1<br>የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰተ ዕርገት።<br>የኢየሱስ መሲሕ ዜና መስቀል፡ በግሼን ማርያም የሚነገርበት | ፳፪ 2 | ፳፫ 3 | ፳፬ 4<br>ኪዳነ መልከ-ጼዴቅ | ፳፭ 5<br>ዮናስ ነቢይ። የክረምት የዝናም) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 6<br>የመፀው (የጽጌ= የአበባ) ወራትና የጽጌ ማሕሌት መግቢያ |
| ፳፯ 7<br>የጽጌ ማሕሌት። | ፳፰ 8<br>ኪዳነ ኣብርሃም | ፳፱ 9 | ፴ 10 | ማስታወሻ:- | | |

"ወፈለግ ይወጽእ እምቅድሜሁ፡ ከመ ይሥቅያ ለገነት፤ ወእምህየ ይትፈለጥ፡ ለአርባዕቱ መአዝነ ዓለም። ...ወስሙ ለካልእ ፈለግ፡ 'ግዮን'፤ ወውእቱ ዘየዐውድ ኵሎ ምድረ-ኢትዮጵያ። ...ወነሥኦ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ-እመሕያው ዘገብሮ፣ ወሤሞ ውስተ ገነት፡ ከመ ይትገበራ፣ ወይዕቀባ። ገነትንም ያጠጣ ዘንድ፡ ከፊትለፊቱ፡ ወንዝ ይወጣ ነበር፤ ከዚያም፡ ወደአራቱ የዓለም ማእዘኖች ይከፈላል። ...የኹለተኛውም ወንዝ ስሙ፡ 'ግዮን' ነው፤ እሱም፡ የኢትዮጵያን ምድር፡ ዙሮ የሚያጠጣ ነው። ...እግዚአብሔርም፡ የፈጠረውን ሰው ወስዶ፡ ያርሳት፥ ይቆፍራት፥ ይጠብቃትና ይንከባከባት ዘንድ፡ በገነት ላይ ሾሞ፡ በዚያ ኣኖረው።" [ዘልደት (ዘፍጥ.) ፪፥ ፰-፲፯።]

| | |
|---|---|
| የመስከረም ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.] እና መጽሓፈ ጥበብ። |

# ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ጥቅምት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of T'q'mt (Oct-Nov., 2018). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | ፩ 11 | ፪ 12<br>**ገዳማዊ ሕርያቆስ፡**<br>**የቅዳሴ ማርያም ደራሲ** | ፫ 13 |
| ፬ 14<br>**አጼ አብርሃወአጽብሓ፡**<br>**የቅዱሱ ኪዳን**<br>**ክርስትናን፡**<br>**በኢትዮጵያ ያስፋፉ።**<br>**የጽጌ ማሕሌት።** | ፭ 15 | ፮ 16<br>**ሓና ነቢይት፡**<br>የነቢዩ ሳሙኤል<br>እናት። **ገዳማዊ**<br>**ጰንጠሌዎን**<br>ከ፸ቱ ቅዱሳን<br>፩ዱ። | ፯ 17 | ፰ 18 | ፱ 19<br>**አጼ ዳዊት፡**<br>የጌታችን የኢየሱስ መሲሕን<br>ግማደ-መስቀል፡ ከኢየሩሳ<br>ሌም ያመጣና "ዓባይን<br>እገድባለሁ!" እያለ፡ በዚያ<br>የሚኖሩ ክርስቲያኖችን፡<br>ከእስላሞች ጥቃት ያዳነ። | ፲ 20<br>**ኢየሱስ መሲሕ**<br>**በ፵ ቀኑ፡በእናቱ ዕቅፍ**<br>**ቤተ-መቅደስ የገባበት።**<br>በዓለ-ስምዖን። ሓና ነቢይት።<br>አጼ ፋሲል፡ካቶሊክነትን<br>ተቃውሞ፡ተዋሕዶነትን አጸና፡ |
| ፲፩ 21<br>**የሕፃኑ ኢየሱስና**<br>**የቅድስት እናቱ**<br>**ድንግል ማርያም ስደት**<br>**መታሰቢያ ጾም**<br>**መግቢያ።**<br>**የጽጌ ማሕሌት።** | ፲፪ 22<br>**ወንጌላዊ ማቴዎስ፡**<br>ከ፲፪ቱ ሓዋርያት<br>፩ዱ። ቅዱስ<br>ድሜጥሮስ፡ የቀንና<br>የዘመን አቈጣጠርን<br>ያስተካከለ | ፲፫ 23 | ፲፬ 24<br>**ፊልጶስ ሓዋርያ፡**<br>ኢትዮጵያዊዉን<br>ጃንደረባ አቤሜሌክን<br>ያጠመቀ።<br>ገዳማዊ ዘሚካኤል<br>አረጋዊ፡ከ፸ኙ ቅዱሳን<br>፩ዱ። ገብረ-ክርስቶስ። | ፲፭ 25 | ፲፮ 26 | ፲፯ 27<br>እስጢፋኖስ ቀዳሚው<br>ሰማዕት፡ የሹመቱ<br>መታሰቢያ። ዲዮስቆሮስ<br>ኢትዮጵያዊ፡ የግብፅ ሊቀ-<br>ካህናትና የተዋሕዶ ሃይማኖት<br>ተጋዳይ፥ የአኰቴት- ቍርባን<br>ቅዳሴው ደራሲ። |
| ፲፰ 28<br>**የጽጌ ማሕሌት።** | ፲፱ 29<br>**አጼ ይምራሕ፡**<br>ቀዳሚዎቹን<br>የእስልምና ስደተኞች፡<br>በኢትዮጵያ አስተናግዶ<br>የሸኘውና እነርሱ፡<br>"ነጋሽ" የሚሉት፡<br>ኢትዮጵያዊ ንጉሥ | ፳ 30 | ፳፩ 31 | ፳፪ 1<br>**ወንጌላዊው**<br>**ሉቃስ** | ፳፫ 2 | ፳፬ 3 |
| ፳፭ 4<br>**የጽጌ ማሕሌት።** | ፳፮ 5 | ፳፯ 6 | ፳፰ 7<br>**አማኑኤል።**<br>ገዳማዊ ይማአታ፡ከ፸ኙ<br>ቅዱሳን ፩ዱ። | ፳፱ 8 | ፴ 9 | ማስታወሻ:- |

**"ወይቤሎ እግዚአብሔር አምላኩ ለኖኅ፡- 'ጊዜሁ ለዕጓለ-እመሕያው፡ በጽሓ ቅድሜየ፡ እስመ መልአ ዐመፃ ዲበ ምድር እምኔሆሙ፤ ወናሁ አነ እደመስሶሙ እምድር። ...ባእ አንተ፥ ወኵሉ ቤትከ፡ ውስተ ታቦት፤ እስመ ኪያከ ረከብኩ ጻድቀ በቅድሜየ፡ በዛቲ ትውልድ። ...ወገብረ ኖኅ፡ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር አምላኩ። ...ወዐጸዋ እግዚአብሔር ለታቦት፡ እምአፍአሃ፤ ወኮነ ማየ አይኅ ላዕለ ምድር፡ ፵ መዓልተ፥ ወ፵ ሌሊተ፤ ወመልአ ማይ፤ ወአልዓላ ለታቦት፤ ወተለዓለት እምድር።" "እግዚአብሔር አምላኩ፡ ኖኅን፡ እንዲህ አለው፡- 'በሰው ላይ፡ ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ፡ በፊቴ ደረሰ! ከእነርሱ የተነሣ፡ በምድር ላይ የግፉ ጽዋ ሞልቷልና፤ እነሆ፡ እኔም፡ ከምድር አጠፋቸዋለሁ።...አንተን ግን፡ በዚህ ትውልድ መካከል፡ በፊቴ፡ እውነተኛ ሰው ኾነህ አግኝቼሃለሁና፡ አንተ፡ ከቤተሰብህ ኹሉ ጋራ፡ ወደመርከብ ግባ!' ኖኅም፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። ...እግዚአብሔርም፡ መርከቧን፡ በውጭ በኩል ዘጋት፤ በምድር ላይ፡ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት፡ የጥፋት ውኃ ዘነበ፤ ውኃውም መልቶ፡ መርከቢቱን አንሳፈፋት፤ ምድርንም ለቀቀች።" የጥምቀት ምሳሌ ለኾነው፡ ለመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ የኢትዮጵያ [ቀይ] ባሕርን አቋርጣ፡ አራራት ተራራ ላይ ለማረፍ፡ ከኢትዮጵያ ተነሣች። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፮፥ ፩-፲፫፤ ፯፥ ፩-፳፬።)**

| የጥቅምት ወር ምንባብ፡- | መጽሓፈ ሩት እና መጽሓፈ ሲራክ። |
|---|---|

# ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ኅዳር ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of H'dar (Nov.-Dec., 2018). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፋት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | | ፩ 10<br>ነአኵቶ ለአብ፡ መንግሥቱን፡ በኢትዮጵያዊው የመልከ-ጼዴቅ ሥርዓት የመራ አጼ። |
| ፪ 11<br>የጽጌ ማሕሌት ፍጻሜ። | ፫ 12 | ፬ 13 | ፭ 14<br>ለንጊኖስ፡ አምላካችን ኢየሱስ መሲሐን ተሰቅሎ ሣለ፡ ጎኑን፡ በጦር የወጋና ኋላ አምኖ፡ በሰማዕትነት የተጋደለ ። የስደት ጾም ማብቂያ። | ፮ 15<br>ቍስቋም፡ ሕፃኑ ኢየሱስ እና ቅድስት እናቱ፡ በስደት የቆዩባት የኢትዮጵያ ገዳም መታሰቢያ በዓል | ፯ 16 | ፰ 17<br>አርባዕቱ እንስሳ። መንበረ ሥላሴን የሚሸከሙ ሕያዋን ፍጡራን (፬ቱ:- ሰው፥ ላሕም፥ አንበሳና ንሥር) |
| ፱ 18<br>ስለአርዮስ ኑፋቄ፡ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤ፡ በኒቅያ | ፲ 19 | ፲፩ 20<br>ቅድስት ሓና ኢትዮጵያዊት፡ የድንግል ማርያም እናት | ፲፪ 21<br>ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ-መላእክት። አጼ በእደ-ማርያም፡ ሃይማኖታዊው ተጋዳይ | ፲፫ 22<br>አእላፍ መላእክት | ፲፬ 23<br>በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. በደርግ የዓመፅና የክህደት አገዛዝ፡ በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ላይ የግፍ ግድያ ተፈጸመ | ፲፭ 24 |
| ፲፮ 25<br>የጾመ-ነቢያት መግቢያ | ፲፯ 26<br>ዓዲስ አበባ ከተማ በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም. የተቈረቈረችበት። | ፲፰ 27<br>ፊልጶስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ 30<br>ኪዳነ ሙሴ። ሕፃን ማርያም፡ በ፫ ቀኗ፡ በቤተ መቅደስ በጌታ ፊት የቀረበችበት። ማርያም ጽዮን። ማክዳ ንግሥትና ልጇ ምኒልክ። | ፳፪ 1 |
| ፳፫ 2<br>ቆርነሌዎስ ጻድቅ (የሓዋ. ምዕ. ፲)<br>፴ 9<br>ገብረ መስቀል (አጼ) በዘመኑ የቅዱስ ያሬድ ሙያና የ፱ኙ ቅዱሳን ዜና የገነነበት። የጾመ-ነቢያት ማብቂያ | ፳፬ 3<br>፳፬ቱ ካህናተ-ሰማይ | ፳፭ 4<br>መርቆሬዎስ ሰማዕት | ፳፮ 5<br>በናግራን (የመን)፡ ኢትዮጵያውያን/ያት ሰማዕታት። በዚያ፡ የአጼ ካሌብ ድል። ኢየሱስ-ሞዐ ዘሓይቅ | ፳፯ 6<br>ገዳማዊ ሊቃኖስ ኢትዮጵያዊ፡ ዘደብረ-ቍንጽል። | ፳፰ 7<br>ገዳማዊ ሊቃኖስ፡ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ። | ፳፱ 8<br>የሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስ ደቀ-መዝሙር፡ ቀሌምንጦስ። የሰማዕታት መጨረሻ ጴጥሮስ። |

**"ወመልከ-ጼዴቅ አምጽአ ኅብስተ፥ ወወይነ፤ ወካህኑ ለእግዚአብሔር ልዑል፤ ወንጉሠ ሳሌም ውእቱ። ወባረኮ ለአብራም፤ ወይቤሎ፡- 'ቡሩኩ አብራም ለእግዚአብሔር ልዑል፤ ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ! ወቡሩክ እግዚአብሔር ልዑል፡ዘአግብአ ለጸላእትከ፡ ውስተ እዴከ! ወወሀቦ አብራም፡ ዐሥራተ ዕድ፡ እምኵሉ።'** መልከ-ጼዴቅም፡ የኅብስትና የወይኑን ቍርባን አመጣ፤ እርሱም፡ የገናናው እግዚአብሔር አገልጋይ፥ የሳሌምም ንጉሥ ነው። አብራምንም፡- 'አንተ፡ ሰማይንና ምድርን ለፈጠረው፡ ለገናናው እግዚአብሔር የተባረክህ ነህ! ጠላቶችህን፡ በእጅህ የጣለልህ ገናናው እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው!' ብሎ ባረከው። አብራምም፡ ከገንዘቡ ኹሉ፡ አሥራትን ሰጠው።" **የእስራኤል ልጆች አባት የኾነውን፡ አብርሃምን፡ ለመለኮታዊው የግርዛት ቃል ኪዳን ያበቃው፡ የኢትዮጵያ ልጆች አጼ የኾነው፡ የዚህ፡ የኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ የክህነት አገልግሎትና ቡራኬ መኾኑን ማስተዋል ነው። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፬፥ ፲፰-፳)**

| | |
|---|---|
| የኅዳር ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘፀአት እና ትንቢተ ኤርምያስ። |

# ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ታኅሣሥ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of Tah'sas (Dec., 2018-Jan, 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበተ ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ 10<br>**በዓለ ትስብእት፥**<br>ኢየሱስ መሲሕ የተፀነሰበት። ብሥራተ ገብርኤል። ኤልያስ ነቢይ። ቤትሳባ ኢትዮጵያዊት የሰሎሞን እናት። | ፪ 11 | ፫ 12<br>**ሕፃን ማርያም፥**<br>በስእለት፥ ለቤተ-መቅደስ የተሰጠችበት። ቅዱስ ፋኑኤል ሊቀ-መላእክት። ዳግማዊ አጼ ምኒልክ። ሀብተ-ጊዮርጊስ፥ አባ መላ። | ፬ 13<br>እንድርያ፥ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፭ 14<br>የቅዱሱ ኪዳን ማስጠንቀቂያ ኾኖ፥በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.፥ በክብር ዘበኛ ጦር አዛዥ የተመራው፤ ብዙ ደም ያፈሰሰው ያልጋ ግልበጣ ሙከራ። | ፮ 15<br>የዓዲስ ዓለም ማርያም ሰማዕታት ካህናት፤ በ፲፱፻፴፫ዓም በፋሺስት ጣልያን የተሠየፉት። |
| ፯ 16<br>**ስብከት።**<br>ፅንሰታ ለማርያም (ድንግል ማርያም የተፀነሰችበት) | ፰ 17<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ኪሮስ | ፱ 18<br>ገዳማዊ በኣሚን ኢትዮጵያዊ | ፲ 19<br>በወሎ፥ ደብረ እግዚአብሔርና የሓይቅ መካነ-እስጢፋኖስ፥ በአሕመድ ግራኝ ጦር ተበዘበዙ። | ፲፩ 20 | ፲፪ 21<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ሳሙኤል፥ የዋልድባው | ፲፫ 22 |
| ፲፬ 23<br>**ብርሃን።**<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የፋሺስት ጣልያን አየር ኃይል በኢትዮጵያ ላይ፥ የመርዝ ጢስ ማዝነብ ጀመረ። | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 | ፲፯ 26 | ፲፰ 27<br>በአኵስሙ ሊቀ-ካህናት እንበረም ተልኮ፥ ያልታሰበውን የግብፅን የጵጵስናን አገዛዝ ወደኢትዮጵያ ያመጣ ፍሬምናጦስ። | ፲፱ 28<br>**ቅዱስ ገብርኤል፥**<br>፫ቱ ደቂቅን፥ ከባቢሎን እሳት አዳነ። | ፳ 29 |
| ፳፩ 30<br>**ኖላዌ።** | ፳፪ 31 | ፳፫ 1<br>**ኪዳነ ዳዊት** | ፳፬ 2<br>የእቲሳው እጨጌ ተክለ-ሃይማኖት ልደት። | ፳፭ 3<br>**የመፀው** (የጽጌ) ወራት ማብቂያ። | ፳፮ 4<br>**የሓጋይ**<br>(የበጋ) ወራት መግቢያ። | ፳፯ 5<br>ኣጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ። |
| ፳፰ 6 | ፳፱ 7<br>የቅዱስ አጼ ላልይበላል ልደት። | ፴ 8<br>ከተራ*፥[የጋድ ጾም] | ማስታወሻ፥-<br>*ከተራ፥ ለጥምቀት በዓል ዋዜማ፥ ውኃ፥ ከወንዝ ተወስዶ የሚከተርበት (የሚጠራቀምበት)። | | | |

ኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ ከባረከው በኋላ፥ እግዚአብሔር ተገልጦለት፥ "**አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፈጣሪከ፥ ዘሖርኩ ቅድሜከ! አሥምር ቅድሜየ! ወኩን ንጹሓ! ወእሠይም ኪዳነ፥ ማእከሌየ ወማእከሌከ! ወአብዝኀከ ጥቀ! ...ወኢይሰመይ እንከ ስምከ 'አብራም'፤ አላ፥ 'አብርሃም' ይሰመይ! እስመ አበ ብዙኃን አሕዛብ ረሰይኩከ።** በፊትህ የኼድሁ ፈጣሪህ እግዚአብሔር፥ እኔ ነኝ! በፊቴ፥ በጎ ነገር ኣድርግ! ንጹሕ ኹን! በእኔ እና በኣንተ መካከል ኪዳንን እሠይማለሁ! እጅግም ኣበዛሃለሁ!...እንግዴህም፥ ስምህ፥ 'አብራም' ኣይባልም፤ 'ኣብርሃም' እንጂ። ለብዙዎች ኣሕዛብ፥ ወላጅ ኣድርጌሃለሁና።" ያለው፥ ይህ የሃይማኖትና የምግባር ሰው፥ ከተገረዘና ሣራ ከሞተች በኋላ፥ ኢትዮጵያዊቷን ኬጡራን፥ በሚስትነት ኣግብቶ፥ "**ምድያማውያን**" የተባሉ፥ የኢትዮጵያን ልጆች በመውለዱ፥ ለኢትዮጵያዊነት፥ ኣንዱ ኣብነት ኾኗል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፯፥ ፩-፳፤ ፳፤፳፭።)

| የታኅሣሥ ወር ምንባብ፥- | መጽሓፈ ሳሙኤል እና ትንቢተ ሕዝቅኤል። |
|---|---|

## ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ጥር ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of TT'rr (Jan.-Feb., 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunda | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ 9<br>**ጥምቀት በዓለ አስተርእዮ**<br>ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አቤሜሌክ [ባኮስ]። በቅዳሴ ጸሎቱ፡የጥምቀት ወንዝ የቆመለት የተጐለቱ ታቦት-ዋሻ ካህን፡ ትልቁ ቀሲስ ወልደ-ኢየሱስ። | ፪ 10<br>**አቤል ጻድቅ** | ፫ 11<br>ገዳማዊ መጣዕ ዘሊባኖስ ኢትዮጵያዊ | ፬ 12<br>ወንጌላዊ ዮሓንስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት፡ ፩ዱ። |
| ፭ 13 | ፮ 14<br>ኖኅ።<br>ዕርገተ ኤልያስ | ፯ 15<br>**የአስተርእዮ ቅድስት ሥላሴ** | ፰ 16 | ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 |
| ፲፪ 20<br>**ድንግል ማርያም፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻት፥ ልጇም ኢየሱስ፡ እውነተኛው መሲሕ መኾናቸው፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ በዓል ተገለጠ።** | ፲፫ 21<br>**ሕንደቄ** ንግሥተ-ኢትዮጵያ፡ በ፴፬ ዓ.ም. በጃንደረባዋ አማካይነት፡ ክርስትና ወዳገርዋ መጣ። | ፲፬ 22<br>**እንበረም** ሊቀ-ካህናት ዘአኵስም በ፫፻፳፭ ዓ.ም. የኢትዮጵያን ሥርዓተ-ቤተ ክርስቲያን አሟላ። | ፲፭ 23<br>ቂርቆስ፡ የ፫ ዓመት ሕፃን ሰማዕት። | ፲፮ 24<br>ኢየሉጣ ሰማዒት፤ የሕፃኑ ቂርቆስ እናት | ፲፯ 25<br>እስጢፋኖስ እንደመምህሩ ፡ኢየሱስ መሲሕ፡ ለእውነት፡ በይፋ መስክሮ የተሠዋ ቀናዒ ካህንና ቀዳሚ ሰማዕት። | ፲፰ 26<br>ዝርወተ ዐፅሙ ለጊዮርጊስ |
| ፲፱ 27<br>መርዓዊ | ፳ 28 | ፳፩ 29<br>**የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰት፡ ወደገነት።** | ፳፪ 30 | ፳፫ 31 | ፳፬ 1 | ፳፭ 2 |
| ፳፮ 3 | ፳፯ 4<br>**ዕርገተ-ሄኖክ** | ፳፰ 5<br>**የበዓለ ኢትዮጵያ መግቢያ።** | ፳፱ 6<br>**በዓለ ኢትዮጵያ።** | ፴ 7<br>**የበዓለ ኢትዮጵያ ማብቂያ።** | ማስታወሻ:- | |

ሙሴ፡ከግብፅ፡ በስደት፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ ስለኢትዮጵያዊነት፡ ከኢትዮጵያዊው ካህን፡ ከዮቶር ተምሮ፡ ካመነ በኋላ፡የካህኑን ሴት ልጅ፡ ሲጳራን አገባ፤ የአማቱን በጎች ሲጠብቅ ሣለም፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር ተገልጾለት፡ ያዘዘውን ኹሉ በመፈጸሙ፡ ኢትዮጵያዊነትን መቀበሉ፡ እውን ኾኗል። ከዚህ ኢትዮጵያዊነቱ የተነሣም፡ የኋላ ኋላ፡ በወንድሙና በእኅቱ ሳይቀር፡ ከእስራኤል ሕዝብ፡ በደል እንደደረሰበት ተጽፏል። ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ፡ ገና፡ በምድረ-በዳ ሠፍረው ሣሉ፡ ጽላተ-ሕጉንና ታቦቱን ከእግዚአብሔር ከመቀበሉ በፊት፡ የሚቃጠልንና ሌላ መሥዋዕትን፡ ለእግዚአብሔር በማቅረብ፡ ሥርዓተ-ክህነትን፥ ስለሕዝብ አስተዳደርና ስለፍትሕ አሰጣጥም በማስተማር፡ የኢትዮጵያን እግዚአብሔራዊ ሥርዓተ-መንግሥት፡ አማቱ፡ ኢትዮጵያዊው ዮቶር፡ ለሙሴና ለአሮን፥ ለሕዝቡ ሽማግሌዎችም ኹሉ ማሳየቱ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግቧል። (ዘጸአ. ፫፥ ፩-፭፤ ፲፰፥ ፩-፳፯። ዘኍል. ፲፪፥፩-፲፭።)

| የጥር ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ኢዮብ እና የማቴዎስ ምሥራች። |
|---|---|

# ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ የካቲት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of Yekkatit (Feb.-Mar., 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 8<br>ስለመቅዶንዮስ ኑፋቄ፡ የ፻፶ ሊቃውንት ጉባኤ በቍስጥንጥንያ። | ፪ 9 |
| ፫ 10<br>የግሼን ማርያም ኣምባ፡ በ፲፭፻፴፪ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር ተመዘበረ። | ፬ 11<br>ጣይቱ ብጡል፡ ብርሃን ዘኢትዮጵያ። | ፭ 12 | ፮ 13<br>ማርያም እንተ ዕፍረት፣ መሲሕን በእንባዋ እግሩን ያጠበች። | ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16 |
| ፲ 17<br>ዘወረደ (ቅበላ)<br>ያዕቆብ ወልደእልፍዮስ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፲፩ 18<br>የዓቢይ ጾምና የጾመ ሕርቃል መግቢያ። | ፲፪ 19<br>በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. የፋሺስት ጣልያን ጦር፡ በሰላማዊው የዓዲስ ኣበባ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግድያና ዕልቂት። | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23<br>ኪዳነ ምሕረት፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ መሲሕ የተገኘ። የቅዱሱ ኪዳን ጥበቃ፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. የጎግ ማጎግ የሱማሌ ወረራ ካራማራ ድል ላይ በገሃድ ታየ። |
| ፲፯ 24<br>ቅድስት። | ፲፰ 25<br>የመሲሕ ኢየሱስ የአርባ ቀን ጾም መነሻ።<br>ኣዝማች ደገልሓን፣ የአሕመድ ግራኝን ጦር፡ በቆራጥነት የተዋጋ ጀግና ኢትዮጵያዊ። | ፲፱ 26 | ፳ 27 | ፳፩ 28<br>ከጉዲት አገዛዝ በኋላ፡ በ፱፻፴፫ ዓ.ም. በአገዉ (በዛጔው) መርሓ-ተክለ ሃይማኖት፡ የኢትዮጵያ መልከ ጼዴቃዊ ሥርዓተ-መንግሥት ተመለሰ። | ፳፪ 1 | ፳፫ 2<br>ኢትዮጵያ፡ ኃይሏ፡በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት፡ የአድዋ ድል። |
| ፳፬ 3<br>ምኵራብ። | ፳፭ 4 | ፳፮ 5 | ፳፯ 6<br>ግራኝ አሕመድ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. ድል ኾነ። | ፳፰ 7 | ፳፱ 8 | ፴ 9 |

"ይሁዳ፡ ዕጓለ-አንበሳ! እምኀዝአትከ ዕርግ! ወልድየ! ሰከብከ፤ ወኖምከ፡ ከመ አንበሳ፥ ወከመ ዕጓለ-አንበሳ፡ አልቦ ዘያነቅሐከ። ኢይጠፍእ ምልክና፡ እምይሁዳ፤ ወምስፍና፡ እምአባሉ፣ እስከ አመ ይረክብ፡ ዘጽኑሕ ሎቱ። ወውእቱ፡ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ። ...ወብዙኃን እለ በከዩ፤ ወአንሂ ምስሌሆሙ፤ እስመ አልቦ ዘተረክበ፡ ዘይደልዎ ይክሥታ፥ ወይርአያ፡ ለይእቲ መጽሐፍ፡ [እንተ ሀለወት] ውስተ የማኑ፡ ለውእቱ፡ዘይነብር ዲበ መንበር። ወይቤለኒ፡ ኣሓዱ፡ እምውስተ እልክቱ [፳፬ቱ] ሊቃናት፡- 'ኢትብኪ! ናሁ፡ ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ፣ እምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፣ ከመ ይፍትሓ፡ ለይእቲ መጽሓፍ፥ ወለማኅተሚሃ!' የይሁዳ ኣንበሳ ደቦል! ከመደብህ ውጣ! ልጄ! እንደአንበሳ ተኛህ፤ አንቀላፋህም፤ እንደአንበሳ ደቦልም፡ ሊቀሰቅስህ የሚችል የለም። መንግሥት፡ ከይሁዳ፥ የሕዝብ አስተዳደርም፡ ከወገኑ አይወጣም፤ ይህ ሥልጣን፡ የሚጠበቅለትን፣ ለአሕዛብም ተስፋቸው የኾነውን፡ እርሱን እስከሚያገኝበት ጊዜ ድረስ። ...በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው፡ በቀኝ እጁ ያለችውን መጽሓፍ ሊዘረጋ፥ ሊመለከታትም የሚገባው፡ ማንም ስላልተገኘ፡ ብዙዎች አለቀሱ፣ እኔም ዓብሬአቸው አለቀስሁ። ከእነዚያ [ከ፳፬ቱ] ሊቃናት መካከል፡ አንዱ፡- 'አታልቅስ! እነሆ፡ ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፣ እርሱም፡ የዳዊት ሥር፡ መጽሓፏን ይዘረጋ ዘንድ፥ ማኅተሟንም ይፈታ ዘንድ፡ ድል ነሥቷል!' አለኝ።" የሚለውን፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በሃይማኖት ተቀብለው፡ በምግባር ስለፈጸሙት፡ እውነተኞቹ እስራኤል እነርሱ መኾናቸው ተረጋግጧል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፵፱፥ ፱-፲፤ ራእ. ፭፣ ፩-፭።)

| | |
|---|---|
| የየካቲት ወር ምንባብ:- | አሪት ዘዳግም፥ ትንቢተ ዮናስና የማርቆስ ምሥራች። |

## ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ መጋቢት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of Meggabit (Mar.-Apr., 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 10<br>**መጻጉዕ።**<br>አጼ ዮሓንስ ፬ኛ<br>የመተማው ሰማዕት<br>በድርቡሽ እስላም<br>ወራሪ የተሠየፈ **አጼ።** | ፪ 11 | ፫ 12 | ፬ 13 | ፭ 14<br>**ገብረ መንፈስ**<br>**ቅዱስ ገዳማዊ** | ፮ 15 | ፯ 16 |
| ፰ 17<br>**ደብረ ዘይት።**<br>ማትያስ፡ ከ፲፪ቱ<br>ሓዋርያት ፩ዱ። | ፱ 18 | ፲ 19 | ፲፩ 20<br>ገዳማዊ አሌፍ፡<br>ከ፱ኙ ቅዱሳን<br>፩ዱ። | ፲፪ 21 | ፲፫ 22 | ፲፬ 23 |
| ፲፭ 24<br>**ገብር ኄር።** | ፲፮ 25 | ፲፯ 26 | ፲፰ 27 | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ 30 |
| ፳፪ 31<br>**ኒቆዲሞስ።** | ፳፫ 1<br>ዳንኤል ነቢይ። | ፳፬ 2<br>ንግሥት ዘውዲቱ<br>ምኒልክ። | ፳፭ 3<br>የሓጋይ<br>(የበጋ)ወራት<br>ማብቂያ | ፳፮ 4<br>የጸደይ<br>(የበልግ)<br>ወራት<br>መግቢያ | ፳፯ 5<br>**አጼ**<br>**ገላውዴዎስ፡**<br>ኰትልክናን፡<br>በተዋሕዶነት<br>የተቋቋመ፤<br>በእስላም ወራሪ፡<br>ሰማዕትነትን<br>የተቀበለ። | ፳፰ 6<br>ቈስጠንጢኖስ ቄሣር፡<br>ስለሃይማኖትና<br>ስለፍትሓ-ነገሥት<br>ዝግጅት፡ የ፫፻፲፰<br>ሊቃውንት ጉባኤን፡<br>በኒቅያ አሰባሰበ። |
| ፳፱ 7<br>**ሆሣዕና።** | ፴ 8<br>የሰሙነ ሕማማት<br>መግቢያ። | ማስታወሻ፡- | | | | |

**"'ናሁ ይመጽእ መዋዕል!' ይቤ እግዚአብሔር፤ 'ወአቀውም ለዳዊት፡ ሠርፀ ጽድቅ፤ ወይነግሥ ንጉሥ፡ ዘይሔሊ፤ ወይገብር ጽድቀ፥ ወርትዐ፡ በዲበ ምድር። ...ወይሠርፅ ጽድቅ፡ በመዋዕሊሁ፤ ወብዙኀ ሰላም፡ እስከ የኀልፍ ወርኅ። ወይኴንን እምባሕር፡ እስከባሕር፤ ወእምአፍላግ፡ እስከአጽናፈ ዓለም። ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ፤ ወጸላእቱሂ፡ ሐመደ ይቀምሑ። ...እግዚአብሔርሰ፡ ንጉሥ ውእቱ፡ እምቅድመ ዓለም፤ ወገብረ መድኃኒተ በማእከለ ምድር። ...አንተ ሰበርከ ርእሱ፥ ወቀጥቀጥከ አርእስቲሁ ለከይሲ። ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ፡ ለሕዝበ ኢትዮጵያ።** 'እነሆ፡ ለዳዊት፡ የእውነት ቍጥቋጥ የማስነሣበት ጊዜ ይመጣል! እርሱም፡ በምድር ላይ፡ እውነትንና ቅንነትን የሚያስብና የሚያደርግ ንጉሥ ይኾናል!' ይላል እግዚአብሔር። ...በዘመኑ፡ እውነት ትከሠታለች፤የግብዝነቱም ወራት አልፎ፡ ሰላም ይበዛል። ከባሕር እስከባሕር፥ ከታላላቁ ወንዞች፡ እስከምድር ዳርቻ ያለውን ዓለም ያስተዳድራል። <u>**የኢትዮጵያ ልጆች፡ ዜጎቹ ይኾናሉ**</u>። ጠላቶቹም፡ አፈር ይበላሉ። ...እግዚአብሔርማ፡ ከዓለም አስቀድሞ፡ ንጉሥ ነው! በምድርም መካከል፡ መድኃኒትን አደረገ። ...አንተ፡ የእባቡን ራስ ሰበርህ! ራሶቹንም፡ ቀጠቀጥህ! <u>**ለኢትዮጵያ ሕዝብህም፡ ሲሳያቸውን ሰጠሃቸው!**</u>(ኤር. ፳፫፥ ፭። መዝ.፸፩፥ ፯-፱፤ ፸፫፥ ፲፪-፲፬)

| | |
|---|---|
| የመጋቢት ወር ምንባብ፡- | ትንቢተ-ኢሳይያስ እና የጳውሎስ መልእክታት። |

# ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ሚያዝያ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of Miazia (Apr.-May, 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunda | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturda<br>y |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | ፩ 9 | ፪ 10<br>የአይሁድ ሸንጎ፡ ኢየሱስ መሲሕን ለመግደል ወሰነ። | ፫ 11<br>ጸሎተሓሙስ። | ፬ 12<br>**የኢየሱስ መሲሕ መስቀለ-ሞቱ።**<br>አዳም ሓሙስ፡ (የ፭ሺ ፭፻ው ዓመት ተስፋ፡ ፍጻሜ። | ፭ 13<br>**ኢየሱስ መሲሕ በመቃብር ያረፈባት ታላቋ ሰንበት።**<br>ሕዝቅኤል ነቢይ። |
| ፮ 14<br>**የኢየሱስ መሲሕ በዓለ ትንሣኤ።**<br>**ዳግማዊ ቴዎድሮስ**<br>አርበኛው አጼ። | ፯ 15<br>ኢትዮጵያዊው ኢያቄም፡ የድንግል ማርያም አባት። | ፰ 16<br>**ማርቆስ ወንጌላዊ** | ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 | ፲፪ 20<br>ደብረ-ብርሃን፡ በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ተቃጠለ። |
| ፲፫ 21<br>**ዳግም ትንሣኤ ።**<br>ከፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ በኋላ ያለው የፍጻሜ ትንሣኤ መታሰቢያ።<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ፋሺስት ጣልያን፡ ማኅበረ ሥላሴን፡ በአየር ኃይሉ ደበደበ። | ፲፬ 22<br>**ማዕዶት**<br>(በሕይወተ-ሥጋ እያሉ በመንፈስ፡ወደትንሣኤ ሕይወት መሻገር) | ፲፭ 23<br>ሦስት የማኅበረ-ሥላሴ ገዳም አባሎች በ፲፱፻፳፰ዓ.ም. በፋሺስት የጣሊያን ጦር ተገደሉ። | ፲፮ 24 | ፲፯ 25<br>ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ፡ ከ ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 |
| ፳ 28 | ፳፩ 29<br>**እጨጌ ዕንባቆም ሰባኬ ሃይማኖት።** | ፳፪ 30 | ፳፫ 1<br>**ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕት** | ፳፬ 2 | ፳፭ 3 | ፳፮ 4 |
| ፳፯ 5<br>ኢትዮጵያ፡ ነጻነቷና በፋሺስት ጣልያን ላይ የተቀዳጀችው ድል፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ ተረጋገጠ። | ፳፰ 6 | ፳፱ 7 | ፴ 8<br>**ርክበ ካህናት** | ማስታወሻ፡- | | |

**"ወንግሥተ ሳባ፡ ሰምዓት ስሞ ለሰሎሞን፤ ወስሞ ለእግዚአብሔር፤ መጽአት ትፍትኖ፡ ምስለ ጥበባ። ወቦአት ኢየሩሳሌም፡ በኃይል ክቡድ ፈድፋደ። ...ወቦአት ኀበ ሰሎሞን፤ ወተናገረቶ ኵሎ ዘሀሎ ውስተ ልባ። ...ወወሀበቶ ለሰሎሞን፡ ምእተ፥ ወዕሥራ መካልየ ዘወርቅ፥ ወአፈዋተ ፈድፋደ ብዙኀ፥ ወዕንቈ ክቡረ፤ ወአልቦ አመ መጽአ ብዙኀ አፈዋተ፡ ዘከመ አሜሃ፡ ዘወሀበት ንግሥተ ሳባ፡ ለሰሎሞን።** የሳባ ንግሥት፡ የሰሎሞንን ስም፥ የእግዚአብሔርም ስም፡ በእርሱ ሲጠራ በሰማች ጊዜ፡ ስለሃይማኖቱና ስለእውነተኛ ማንነቱ፡ በጥበቧ ትፈትነው ዘንድ፡ እጅግ ብዙ ከኾነ ሠራዊትና ጓዝ ጋር፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደኢየሩሳሌም መጣች።...ወደሰሎሞንም ገባች፤ በልቧ ውስጥ ያለውን ኹሉ፡ ገልጣ ነገረችው። መቶ ሃያ የወርቅ መክሊትን፥ እጅግ ብዙ የኾነ ሽቱን፥ የከበረ ዕንቍንም [ሉልን] ሰጠችው። የዚያን ጊዜ፡ የሳባ ንግሥት፡ ለሰሎሞን የሰጠችውን፡ ያን የመሰለ ብዛት ያለው ስጦታ፡ ከዚያ ወዲያ አልመጣም።" የትንቢቱ ፍጻሜና ዘላለማዊው ንጉሥ ኢየሱስ መሲሕ፡ በምድር ላይ በተገለጠበት ጊዜ፡ ከእርሱ፡ ማስረጃ ምልክትን ለጠየቀው፡ ለዚያ፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ክፉና ዘማዊ ትውልድ፡ እንዲህ የሚል የመጨረሻ መልስን ሰጠ፡- "**ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሕ፥ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፡ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፤ ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ሀሎ ዝየ።** ንግሥተ አዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ፡ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።" ከዚህ ፍርድ ለመዳን፡ "**ነገሥተ ምድር ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር! ወዘምሩ ለአምላክነ! ወለኢትዮጵያ፡ ዘታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር።** እናንተ፡ በምድር ያላችሁ የሰዎች መንግሥታት ኹሉ፡ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔርና እጆቿን፡ ወደእርሱ አድርሳ ለምትኖረው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘምሩ! ምስጋናችሁንም አቅርቡ!" (፩ነገ. ፲፥ ፩-፲። ማቴ. ፲፪፥ ፵፪። መዝ. ፷፯፥ ፴፩-፴፪።)

| | |
|---|---|
| **የሚያዝያ ወር ምንባብ፡-** | **ትንቢተ ዳንኤል እና ራእየ-ዮሓንስ።** |

## ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ግንቦት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of G'nbot (May-June, 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | ፩ 9<br>**ቅድስት** ድንግል ማርያም፡ በሊባኖስ ተራራ ላይ የመወለዷ መታሰቢያ | ፪ 10<br>**ኢዮብ ጻድቅ ኢትዮጵያዊ** | ፫ 11 |
| ፬ 12 | ፭ 13<br>ኢትዮጵያውያኑ ኤርምያስ ነቢይ፥ ደቀ-መዛሙርቱ፡ አቤሜሌክና ባሮክ። | ፮ 14<br>ሰሎሜ ቅድስት፡ የደብረ ሊባኖሷ ኢትዮጵያዊት | ፯ 15 | ፰ 16 | ፱ 17<br>ዕሌኒ ንግሥት፡ የመሲሕ ኢየሱስን መስቀል አስቆፍራ አስገኘች። | ፲ 18<br>አናንያ፥ አዛርያና ሚሳኤል በሃይማኖታቸው ጽናት፡ ከባቢሎን እሳት ዳኑ። |
| ፲፩ 19<br>ያሬድ ኢትዮጵያዊው ማሕሌታይ ካህን።<br>ገዳማዊ አሴር፡ የባሌ መምህር። | ፲፪ 20<br>አጼ እስክንድር፡ የእስላምን ወራሪ ጦር ሲከላከል፡ ሰማዕትነትን፡ በወጣትነቱ የተቀበለ። ዮሓንስ አፈወርቅ። | ፲፫ 21<br>የደብረ-ሊባኖስ ገዳም አባሎች፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር ተሠዉ። | ፲፬ 22 | ፲፭ 23<br>**ዕርገት**<br>ናትናኤል፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 |
| ፲፰ 26 | ፲፱ 27 | ፳ 28<br>ቅዱስ አጼ ካሌብ፡ ወደ ናግራን (የመን) ግዛቱ፡ በመርከብ ዘምቶ፡ የአይሁድን አሠቃቂ ወረራ ድል አደረገ። | ፳፩ 29<br>የደርግ፡ የክህደትና የዓመፅ አገዛዝ፡ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተወገደ። | ፳፪ 30 | ፳፫ 31 | ፳፬ 1<br>**ዕንባቆም ነቢይ።** |
| ፳፭ 2<br>**በዓለ መንፈስ ቅዱስ** (በዓለ ሃምሳ)።<br>ቅድስት ሰሎሜ፡ በሕፃኑ ኢየሱስና በቅድስት ድንግል እናቱ ስደት ያልተለየች። | ፳፮ 3<br>**የሓዋርያት ጾም መግቢያ።**<br>ቶማስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፳፯ 4<br>ያዲስ አበባ ሕዝብ ከተቀጣጠሉት የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤቶች፡ የዕልቂት እሳተ ገሞራነት፡ በቅዱሱ ኪዳን የከለላ ኃይል ዳነ። | ፳፰ 5<br>**የጾመ- ድኅነት** (የረቡዕና ዓርብ ጾም) መነሻ። | ፳፱ 6<br>ገዳማዊ አፍጼ እና ገዳማዊ ጉባ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፪ቱ። | ፴ 7 | ማስታወሻ:- |

ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ወደመቅደስ ወጥቶ ሲያስተምር፡ ሊገድሉት ለሚፈልጉት አይሁድ፡ **"ኢትፍትሑ፡ በአድልዎ ገጽ! አላ፡ ፍትሐ-ጽድቅ ፍትሑ! ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ፡ መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!"** አላቸው። ለምን እንዲህ አላቸው? "መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" የሚለው የጌታ ቃል፡ ቀድሞ፡ በሙሴ ላይ፡የተነሣሣባቸው ቅንዓት የተከሠተው፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በሲጳራ ምክንያት እንደነበረ ኹሉ፡ አኹን ደግሞ፡ በእርሱ፡ በኢየሱስ መሲሕ ኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀጣጠለ መኾኑን ሲያመለክታቸው እንደኾነ፡ ማስተዋል ነው። **"'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።** ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" ሲል፡ ነቢዩ አሞጽ የተናገራቸውን ቃላት፡ በዚያን ጊዜም፡ አይሁድ አላስተዋሏቸውም። (ዮሓ. ፯፥ ፲፬-፳፬። ዘኍል. ፲፪፥ ፩-፲፮። አሞ. ፱፥ ፯።)

| የግንቦት ወር ምንባብ፡- | መጻሕፍተ አስቴር፥ ምሳሌ እና መክብብ። |
|---|---|

## ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ሰኔ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of Seney (June-July, 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሐሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | | ፩ 8<br>ወንድሞቹ የሸጡት የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍና ኢትዮጵያዊት ሚስቱ አስናት። |
| ፪ 9 | ፫ 10 | ፬ 11 | ፭ 12 | ፮ 13<br>በፋሺስት ጣልያን የታጠቀ፣ የተመራም፡ የራያ እስላም፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. የሸዋ ቆላ ኢትዮጵያውያንን፡ በሰለባ ጭምር ፈጀ። | ፯ 14 | ፰ 15 |
| ፱ 16<br>ሳሙኤል ነቢይ። | ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19<br>ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ-መላእክት።<br>አጼ ላልይበላል። | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 |
| ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>ገዳማዊ ገሪማ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ። | ፲፰ 25 | ፲፱ 26 | ፳ 27<br>ሕንጸታ፡በአዳምና ሔዋን ኪዳነ ሰብሳብ፡ በኢትዮጵያ የተመሠረተችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በድንግል ማርያም እና በኢየሱስ መሲሕ ኪዳነ-ምሕረት፡ በኢየሩሳሌም ተገለጠች። ኤልሳዕ ነቢይ። | ፳፩ 28<br>በቅዱሱ ኪዳን ላይ ክህደትና ዓመፅ የፈጸመውን የኢትዮጵያ ትውልድ ሊቀጣ የተላከው ደርግ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ተቋቋመ። | ፳፪ 29 |
| ፳፫ 30<br>ሰሎሞን ንጉሥ፡ የምኒልክ አባት | ፳፬ 1<br>ሙሴ (ጸሊም) ኢትዮጵያዊ | ፳፭ 2<br>ያስቆሮቱ ያይደለ ሓዋርያው ይሁዳ።<br>የጸደይ (የበልግ) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 3<br>ኢያሱ ወልደ-ነዌ።<br>የክረምት (የዝናም) ወራት መግቢያ | ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6<br>ቀዳማዊ ቴዎድሮስ በሺ፬፻፬ ዓ.ም. የተቀባው ስመ ጥሩው ጻድቅ አጼ። |
| ፴ 7<br>የላስታ ላልይበላል [ላሊበላ] አብያተ ክርስቲያን በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር ተበዘበዙ። | ማስታወሻ:- | | | | | |

"ወነበቦ መልአከ-እግዚአብሔር፡ ለፊልጶስ፤ ወይቤሎ:- 'ተንሥእ! ወሑር፡ ጊዜ ቀትር፣ ፍኖተ በድው፡ ዘያወርድ፡ እምኢየሩሳሌም፡ ለጋዛ! ወተንሥአ፤ ወሖረ፤ ወረከበ፡ ብእሴ፡ እምሰብአ ኢትዮጵያ፣ ኀፅዋ ለሕንደኬ፡ ንግሥተ-ኢትዮጵያ፥ ወመጋቢሃ ውእቱ፡ ላዕለ ኵሉ መዛግብቲሃ። ወሖረ ኢየሩሳሌም ይስግድ። ወእንዘ ይገብእ፡ ነበረ ዲበ ሠረገላሁ፤ ወያነብብ፡ መጽሓፈ ኢሳይያስ ነቢይ። ወይቤሎ መንፈስ ቅዱስ ለፊልጶስ።- 'ሑር! ትልዎ፡ ለዝ ሠረገላ!' ...ወይቤሎ ኅፅው፥ ...ወአስተብቍዖ ለፊልጶስ፡ ከመ ይዕርግ፥ ወይንበር ኀቡረ ምስሌሁ። የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፊልጶስን፡ 'በቀትር ጊዜ ተነሥተህ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደጋዛ ወደሚያወርደው፡ የምድረ-በዳ መንገድ ኺድ!' አለው። ተነሥቶም ኼደ። እነሆም፡ ከኢትዮጵያ ሰዎች የኾነ አንድ ሰውን አገኘ። እርሱም፡ 'ሕንደኬ' የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባዋ የኾነ፥ በሀብቷም ላይ ኹሉ የሠለጠነ፡ በዥሮንዲ ነው፤ ወደኢየሩሳሌም መጥቶ፡ ከተሳለመ በኋላ፡ በሠረገላው ተቀምጦ ሲመለስ፡ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሓፍ እያነበበ ነበረ። መንፈስ ቅዱስም፡ ፊልጶስን:- 'ኺድ! ይህን ሠረገላ ተከተል!' አለው። ...ጃንደረባውም፡ ፊልጶስን አናገረው፤ ወደሠረገላው ወጥቶ፡ ከእርሱ ጋር ዓብሮት እንዲቀመጥም ለመነው።" የዓዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ የኾነው ጃንደረባም፡ ወዲያው፡ "ኢየሱስ መሲሕ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደኾነ አምናለሁ!" ስላለ፡ ፊልጶስ፡ እዚያው አጠመቀው። ከጥምቀቱም በኋላ፡ ጃንደረባው አቤሜሌክ፡ በተደረገለት፡ መለኮታዊ የቸርነት ሥራ፥ በተቀዳጀውም፡ ዘለዓለማዊ፡ የመንፈስ ቅዱስ ብፅዕና፡ በደስታ እጅግ ተመሥጦ ስለነበረ፡ ፊልጶስ፡ ከአጠገቡ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነጥቆ የመወሰዱን ተአምር ሳያስተውል፡ ዝም ብሎ፡ የሠረገላ መንገዱን ቀጠለ። (የሓዋ. ፰፥ ፳፮-፴፱።)

| የሰኔ ወር ምንባብ:- | የሓዋርያት ሥራ እና ንኡሳኑ መልእክታት። |
|---|---|

# ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ሓምሌ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of Hamley (July-Aug., 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበተ ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ 8 | ፪ 9<br>ታዴዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፫ 10<br>ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ (የአኩስም ንቡረ-እድ)፤ የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስክር፡ ልደት። | ፬ 11<br>የጾመ-ሓዋርያት ማብቂያ | ፭ 12<br>በዓለ ቅዱሳን ሓዋርያት፡ ጴጥሮስ ወጳውሎስ | ፮ 13<br>ዕርገተ እዝራ |
| ፯ 14<br>ሥሉስ ቅዱስ በአብርሃም ቤት የተገኙበት። በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር በሰማዕትነት የተሠዉት ፳፰ቱ የደብረ-ሊባኖስ ገዳም አባላት። | ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19 | ፲፫ 20 |
| ፲፬ 21 | ፲፭ 22<br>ኤፍሬም፡ የውዳሴ ማርያም ደራሲ | ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>ነቢዩ ዮናስ፡ ነነዌ ገባ። | ፲፰ 25<br>ያዕቆብ፡ በኢየሩሳሌም፡ የቤተ- ክርስቲያን የመጀመሪያው ሊቀ-ካህናትና ሰማዕት። የኢትዮጵያ ልጆች፡ ጦቢያና ጦቢት | ፲፱ 26<br>ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ-መላእክት፡ ሕፃኑን ሰማዕት ቂርቆስንና እናቱን ኢየሉጣን፡ ተጥለውበት ከሚነድድባቸው እሳት አዳነ። | ፳ 2 7 |
| ፳፩ 28<br>አጼ ሠርፀ-ድንግል፡ ሃይማኖታዊው ተጋዳይ። | ፳፪ 29<br>ቅዱስ ዑራኤል፡ ሊቀ-መላእክት። | ፳፫ 30<br>ቅዱስ ጴጥሮስ፡፡ ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ሰማዕት፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት የጣልያን ጦር፡ በግፍ ተገደለ። | ፳፬ 31<br>የደብረ ሊባኖስ ገዳም፡ በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ተቃጠለ። ከገዳሙ አባሎች መካከል፡ እየራሳቸውን፡ ለእሳቱ፡ በሰማዕትነት ማገዱ። | ፳፭ 1<br>ገዳማዊ ሕፃን-ሞአ ኢትዮጵያዊ | ፳፮ 2<br>ጻድቅ ዮሴፍ ኢትዮጵያዊ፡ ሕፃኑን ኢየሱስንና እናቱን ድንግል ማርያምን ለማገልገል በመብቃቱ፡ በፈጣሪ የተመረጠ ጃንደረባ። | ፳፯ 3 |
| ፳፰ 4 | ፳፱ 5 | ፴ 6<br>ማርያም ክብራ (እቴጌ ናዖድ ሞገሳ) የአጼ ናዖድ ሚስት | ማስታወሻ:- | | | |

"ወአንጐርጐሩ አይሁድ በእንቲአሁ፤ እስመ ይቤሎሙ፡- 'አነ ውእቱ፡ ኅብስተ-ሕይወት፤ ዘወረደ እምሰማይ!' ወይቤሉ፡- 'እፎ ይክል ዝንቱ፡ የሀበነ ሥጋሁ ንብላዕ?' እንግዲህ፡ ኢየሱስ፡ 'ከሰማይ የወረደ እንጀራ፡ እኔ ነኝ!' ስላላቸው፡ አይሁድ፡ ስለእርሱ አንጐራጐሩ፤ 'እንዴትስ፡ ይህ ሰው፡ ሥጋውን እንበላ ዘንድ ሊሰጠን ይችላል?' አሉም።" ከዚህ የተነሣ፡ "ወብዙኃን፡ እምአርዳኢሁ፡ እለ ሰምዑ፡ ወይቤሉ፡ 'ዕፁብ ዝንቱ ነገር! ወመኑ ይክል ሰሚዖቶ? ...ወገብኡ ድኅሬሆሙ፤ ወኢሖሩ እንከ ምስሌሁ።' ከደቀ-መዛሙርቱ መካከል ሳይቀር፡ ይህን የሰሙ፡ ብዙዎች፡ 'ይህ፡ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው! ማን ሊሰማው ይችላል?' ብለው፡ እርሱን መከተልን ትተው፡ ወደኋላቸው ተመለሱ።" በዚህ ጊዜ፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ "አማን አማን እብለክሙ! እመ ኢበላዕክሙ ሥጋሁ፡ ለወልደ ዕጓለ-እመሕያው፤ ወኢሰተይክሙ ደሞ፡ አልብክሙ ሕይወት ላዕሌክሙ። ዘበልዐ ሥጋየ፥ ወሰትየ ደምየ፡ ቦ ሕይወት ዘለዓለም። ወአነ አነሥኦ፡ በደኃሪት ዕለት። እውነት እውነት እላችኋለሁ! የማርያምን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ፡ በእየራሳችሁ፡ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን፡ የበላ፤ ደሜንም፡ የጠጣ፡ የዘለዓለም ሕይወት አለው። እኔም፡ በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።" ሲል፡ ሊድን ለሚፈልግ፡ ለዓለሙ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ የመጨረሻ ዓዋጅ የኾነውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ገልጦና አስረግጦ ተናገረ። (የሓ.፮፥ ፵፩-፶፱።)

| የሓምሌ ወር ምንባብ:- | ደቂቀ ነቢያት እና የዮሓንስ ምሥራች። |
|---|---|

# ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ነሓሴ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2011 Era of Mercy. Month of Nehassey (Aug.-Sept., 2019). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thurs day | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ 7<br>የፍልሰታ ለማርያም ጾምና ሱባዔ መግቢያ። ኢየሱስን የገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ። | ፪ 8 | ፫ 9 | ፬ 10 |
| ፭ 11<br>ገዳማዊ ፊልጶስ፡ ዘደብረ-ቢዘን | ፮ 12<br>ማርያም መግደላዊት፡ የመሲሕን ትንሣኤ፡ ቀድማ አይታ፡ አበሠረች። | ፯ 13<br>አጼ ናዖድ የመልክዓ ማርያምና የመልክዓ ኢየሱስ ደራሲ። | ፰ 14 | ፱ 15 | ፲ 16 | ፲፩ 17 |
| ፲፪ 18 | ፲፫ 19<br>**ቡሔ ደብረ-ታቦር፡** ጌታ፡ በግርማ መለኮቱ ታየ። | ፲፬ 20<br>የፍልሰታ ለማርያም ሱባዔ ማብቂያ | ፲፭ 21<br>የፍልሰታ ለማርያም ጾም ማብቂያ | ፲፮ 22<br>**የድንግል ማርያም፡ በዓለ ፍልሰታ። ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በ፳፻፭ ዓ.ም. ራዑን በአዋጅ፤ ለግዙፉ ዓለም በይፋ ገለጠች።** | ፲፯ 23 | ፲፰ 24<br>አዝማች አዳሉ፡ በአሕመድ ግራኝ ወረራ የተሠዋ። |
| ፲፱ 25 | ፳ 26 | ፳፩ 27 | ፳፪ 28 | ፳፫ 29<br>ገዳማዊ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፡ ኢትዮጵያዊው የመዓዛ ቅዳሴና የሰዓታት፥ የሌሎችም ጸሎታት ደራሲ። | ፳፬ 30<br>እጨጌ ተክለ- ሃይማኖት። በ፲፪ኛው ፻ ዓመት፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት፡ ወደሰሎሞናዊው አገዛዝ እንዲመለስ ያስማማ። ክርስቶስ ሠምራ፡ ለኢትዮጵያዊነት አብነት። | ፳፭ 31 |
| ፳፮ 1 | ፳፯ 2<br>አጼ ዓምደ ጽዮን፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተጋደለ | ፳፰ 3<br>አብርሃም፥ ይስሓቅና ያዕቆብ | ፳፱ 4<br>ንዋየ-ክርስቶስ (ኣለቃ ዘካርያስ)፡እስላም ሣለ እስላሞችን፡ በቁርዓናቸው የረታና ብዙዎቹን፡ ያስጠመቀ ኢትዮጵያዊ ሓዋርያ፡ለኢትዮጵያዊነት፡ ኣብነትና ድልድይ የኾነ። | ፴ 5<br>ኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡እርሱም ቅዱሱን ኪዳን፡ ከኖኅ የተረከበው የፊተኛው፤ አብርሃምን በባረከው፡ በማእከላዊው አማካይነት፡ ለመጨረሻውና ለኣማናዊው መልከ ጼዴቅ፡ኢየሱስ መሲሕ ቀዳሚ አርአያ የኾነው። | ጳ ጉ ሜ<br>፩ 6<br>የንስሓ ጾም መግቢያ | ፪ 7 |
| ጳ ጉ ሜ | | | | | | |
| ፫ 8<br>ቅዱስ ሩፋኤል። አጼ ዘርዓ ያዕቆብ | ፬ 9<br>የቅዱሳንና የቅዱሳት ኹሉ ዝክር። | ፭ 10<br>ዓሞጽ ነቢይ። | ፮ 11<br>የንስሓ ጾም ማብቂያ። | | | |

መልአኩ፡ ቅዱስ ገብርኤል፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻትን፡ ድንግል ማርያምን፡ "**ተፈሥሒ ፍሥሕት፡አ ምልዕተ-ጸጋ፡ እግዚአብሔር ምስሌኪ! ቡርክት አንቲ እምአንስት!** ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽው፥ እግዚአብሔርም፡ ካንቺ ጋራ የኾነው፡ አንቺ፡ ጸጋን የተመላሽ፡ ደስተኛዪቱ ሆይ! ደስ ይበልሽ!" ኣላት። መንፈስ ቅዱስ የመላባት ኤልሣቤጥም፡ "**ቡርክት አንቲ እምአንስት! ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ!** ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ ኣንቺ የተባረክሽ ነሽ! የማሕፀንሽም ፍሬ፡ የተባረከ ነው!" ኣለቻት። ራሷ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ "**ታዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር! ወትትሐሠይ መንፈስየ፡ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ! እስመ ርእየ ሕማማ ለአመቱ! ናሁ እምይእዜሰ፡ ያስተበፅዑኒ፡ ኵሉ ትውልድ!** እስመ ገብረ ሊተ፤ ኃይለ ዐቢያተ! ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ ታልቀዋለች! መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ እጅግ ደስ ይላታል! የአገልጋዩን መከራ ኣይቷልና! እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ፡ ያመሰግኑኛል! እርሱ፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ተአምራትን ኣድርጓልና። (ሉቃ. ፩፥ ፳፮-፶፱።)

| የነሓሴ እና የጳጉሜ ወራት ምንባባት:- | መጽሓፈ ጦቢት እና የሉቃስ ምሥራች። |
|---|---|